


**ቁጥር 27/02 ጥቀምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም.**

# *<u>የመስከረም ወር የአየርና የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ሁኔታና ከጥቅምት ወር የአየር ሁኔታ አዝማሚያ አንፃር በአርሶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩና አርብቶ አደሩ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች</u>*

## ሀ. የመስከረም ወር 2002 ዓ.ም የአየርና የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ሁኔታ

### 1. የዓየር ሁኔታ

በመስከረም ወር በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የነበረውን የአየር ሁኔታ አስመልክቶ ከተለያዩ ምንጮች በተገኙና በተተነተኑ መረጃዎች መሰረት እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖ የሰነበተ ቢሆንም ሁኔታው ከወሩ አጋማሽ በኂላ በነበሩት ቀናት ተሻሽሎ ደረቅ የአየር ሁኔታ ሰፍኖ ከቆየባቸው አካባቢዎች አብዛኛዎቹ ከግብርና ስራ እንቅስቃሴ አንፃር ጠቀሜታ ያለው ዝናብ ማግኘታቸው ታውቋል፡፡

በክልሎች የነበረውን የዝናብ ሁኔታ በተመለከተ፡-

- በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ክልል ከፋ፣ ጌዴኦ፣ ሸካ፣ ቤንች ማጂ፣ ዳውሮ፣ ስልጤ ዞኖችና ባስኬቶና የም ልዩ ወረዳዎች ሁሉንም ወረዳዎች/ቀበሌዎች የሸፈነና ስርጭቱ የተስተካከለ ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኙ ሲሆን ጉራጌ፣ ወላይታ፣ ሀዲያ፣ ጋሞጎፋ፣ ደ/አሞ፣ ከምባታ ጠምባሮ ዞኖችና አማሮ፣ ቡርጂ፣ ደራሼ፣ ኮንታ፣ ሀላባና ኮንሶ፣ ልዩ ወረዳዎች ካሉዋቸው ወረዳዎች/ቀበሌዎች ከፊሉን የሸፈነ በአብዛኛው ስርጭቱ ያልተስተካከለ ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኙ መሆናቸው፣

- በትግራይ ክልል ምዕራባዊ፣ ሰሜናዊ ምዕራብ፣ ማዕከላዊ፣ ምስራቃዊ፣ ደቡባዊ ምስራቅና ደቡባዊ ዞኖች ከነሀሴ መጨረሻ ጀምሮ እስከ መስከረም አጋማሽ ድረስ የክረምቱ ዝናብ ተቋርጦ መሰንበቱ፣ ሆኖም ከእነዚህ አካባቢዎች መካከል በደቡባዊ ዞን ራያ አዘቦ፣ እንዳመሆኒ፣ አላማጣ፣ አፍላ፣ ህንጣሎ ዋጅራት ወረዳዎች፣ በማዕከላዊ ዞን አህፈሮም ወረዳ፣ በሰሜን ምዕራብ ዞን አሰገደ ጽምብላ፣ መደባይ ዛና፣ ፀለምቲ ወረዳዎች፣ በምስራቃዊ ዞን ክልተ አውላእሎ፣ አብይአዲና ጋንታ አፈሹም ወረዳዎች ከመስከረም አጋማሽ በኂላ ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ከ1 እስከ 2 ቀናት የተመዘገበ መሆኑ፣ በሌላ በኩል ከደቡባዊ ምስራቅ ዞን እንደርታና ሳዕርቲ ሳምረ ወረዳዎች፣ ከምስራቃዊ ዞን አፅቢ ወንበርታ፣ ሀውዜን፣ ሳዕሲዕ ፃአዳ እምባና ኢሮብ ወረዳዎች በክረምቱ ወቅት ደረቅ የአየር ሁኔታ ሰፍኖባቸወ የሰነበተ መሆኑ፣



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

- በኦሮሚያ ክልል (ምዕራብ፣ ምስራቅና ቄለም) ወለጋ፣ ጂማ፣ ምዕ/ሸዋና ጉጂ ዞኖች ሁሉንም ወረዳዎች የሸፈነ ስርጭቱ የተለያየ ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ማግኘታቸው፣ (ደ/ምዕራብ፣ ሰሜን፣ ምስራቅ) ሸዋ፣ ኢሉአባቦራ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ቦረና፣ ምስ/ሐረርጌና ምዕ/ሐረርጌ ዞኖች ካሉዋቸው ወረዳዎች ከፊሎቹን የሸፈነ በአብዛኛው ስርጭቱ ያልተስተካከለ ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኙ መሆኑ፣

- በአማራ ክልል በወሩ የመጀመሪያው አጋማሽ ውስጥ በኦሮሚያና በአዊ ዞኖች ሁሉም ወረዳዎች፣ በደ/ወሎ ዞን ከለላ፣ ለጋምቦ፣ ቦረና፣ አርጎባ፣ ተሁለደሬ፣ አምባሰልና ተንታ፣ በሰ/ሸዋ ዞን ኤፍራታ፣ ግድም፣ ቀወት፣ አንጾኪያ፣ መንዝና ጌራ፣ በደ/ጎንደር ዞን ፋርጣ፣ እብናት፣ ታች ጋይንት፣ ሊቦ፣ ደራ፣ ፎገራ፣ ሰማዳና ምስ/እስቴ፣ በሰ/ጎንደር ዞን ጣቁሳ፣ ላይ አርማጭሆ፣ ታች አርማጭሆ፣ መተማ፣ ጭልጋ፣ ጠገዴና ደባርቅ፣ በምስ/ጎጃም ዞን ሞጣ፣ መርጦለ ማርያም፣ ደጀን፣ እነብሴ፣ ሸበልና ጎንቻን ጨምሮ በ15 ወረዳዎች፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን ባ/ዳር ዙሪያ፣ ወንበርማ፣ ሰከላ፣ ደጋዳሞትና ሜጫ ወረዳዎች፣

- በሁለተኛው የወሩ አጋማሽ በክልሉ በደ/ወሎ ዞን በሁሉም ወረዳዎች፣ በሰ/ወሎ ዞን ዋድላ፣ መቄት፣ ላስታና ጉባላፍቶ ወረዳዎች፣ በሰ/ሸዋ ዞን 13 ወረዳዎች፣ በደ/ጎንደር ዞን ፋርጣ፣ ምስ/እስቴና ደራን ጨምሮ በአብዛኛዎቹ ወረዳዎች፣ በሰ/ጎንደር ዞን 10 ወረዳዎች፣ በምስ/ጎጃም ዞን እነብሴ፣ ሸበል፣ ጎንቻና ደጀንን ጨምሮ በ10 ወረዳዎች፣ በምዕ/ጎጃም ዞን 13 ወረዳዎች፣ በአዊ ዞን ሁሉም ወረዳዎች እንዲሁም በኦሮሚያ ዞን አብዛኛዎቹ ወረዳዎች ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለውና ስርጭቱ የተለያየ ዝናብ ማግኘታቸውና፣ በዋግ ኽምራ ዞን በወሩ መጨረሻ ከነበረው አነስተኛ ካፊያና ደመና በስተቀር ዝናብ ያልነበረ መሆኑ፣

- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሁሉንም ወረዳዎች ያዳረሰና ስርጭቱ የተስተካከለ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ መመዝገቡ፣

- በጋምቤላ ክልል አብዛኛዎቹን ወረዳዎች ያዳረሰ ነገር ግን ስርጭቱ ያልተስተካከለ አነስተኛ ዝናብ የዘነበ ሲሆን በተለይ ከፊል ላሬ፣ ከፊል አኮቦ፣ ከፊል ጆርና ዋንቱዋ ወረዳዎች የነበረው ዝናብ ከሌሎቹ ወረዳዎች በጣም ያነሰ መሆኑ፣

- በሐረሪ ክልል በወሩ መጨረሻ ሳምንት ሁሉንም ቀበሌዎች ያዳረሰ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበ መሆኑ፣

- በድሬዳዋ አስተዳደር እስከ ወሩ መጨረሻ ድረስ ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ ሰፍኖ የሰነበተ መሆኑ፣

- በሶማሌ ክልል ጂጂጋና ሽንሌ ዞኖች ከሐምሌ እስከ መስከረም ወራት የነበረው የካራን (Karan) ዝናብ በጂጂጋ ዞን የተሻለ ቢሆንም በአጠቃላይ ከመደበኛው በታች መሆኑ፣ በመደበኛ ሁኔታ እ.አ.አ. ከጥቅምት አጋማሽ እስከ ታህሳስ አጋማሽ በክልሉ የሚጠበቀው የዴር (Deyr) ዝናብ ተጠቃሚ ከሆኑት ሰባት ዞኖች (አፍዴር፣ ሊበን፣ ጎዴ፣ ቆራሄ፣ ደገሀቡር፣ ፊቅና ዋርዴር ዞኖች) ውስጥ ዋርዴር፣ ደገሀቡር፣ ሊበን፣ ፊቅና ቆራሄ ዞኖች የተለያዩ ቦታዎች ከጥቅምት ወር መጀመሪያ አካባቢ ጀምሮ ከካፊያ መካከለኛ መጠን እስካለው ዝናብ የተመዘገበ መሆኑ፣



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢ-ሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

- በአፋር ክልል በወሩ የመጀመሪያው አጋማሽ ውስጥ በክልሉ ከሚገኙት ጠቅላላ ወረዳዎች ውስጥ ግማሽ ያህሉ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኙ ሲሆን በወሩ ሁለተኛው አጋማሽ ውስጥ በሚሌ፣ ዳሊፋጌና ደዌ ወረዳዎች መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበ መሆኑን ከየአካባቢው የተሰበሰቡ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡

## 2. የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ሁኔታ

### 2.1. ሰብል ልማት

- ባሳለፍነው መስከረም ወር በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች የነበረው የዝናብ ሁኔታ በአጠቃላይ ሲታይ መደበኛ የሰብል ልማት ተግባራትን ወቅቱን ጠብቆ ለማከናወን አመች ሁኔታ መፍጠሩንና በየአካባቢዎቹ በዘንድሮው መኸር ወቅት የሚጠበቀውን ምርትና ምርታማነት እውን ለማድረግ እገዛ ማድረጉን ከየአካባቢው ከተሰበሰቡት የክትትል መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

- ከሰብል ልማት እንቅስቃሴ አንፃር የተሻለ የዝናብ ሁኔታ በነበረባቸው የተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሰብሎች ቀጣይ እድገት አመች ሁኔታ ከመፈጠሩም በላይ በመደበኛ ሁኔታ በዚህ ጊዜ የሚዘሩ አካባቢዎች የዘር ስራ እንዲያከናውኑ፣ በዝናብ እጥረት ምክንያት በመደበኛ የመዝሪያ ወቅት በዘር ያልተሸፈኑ ማሳዎች እንዲሸፈኑና የተጎዱ ማሳዎች ተገልብጠው ዘግይተው በሚዘሩ ሰብሎች እንዲተኩ እንዲሁም ሌሎች መደበኛ የሰብል ልማት ተግባራት እንዲከናወኑ በወሩ የነበረው ዝናብ እገዛ ማድረጉን፣

- በወሩ የመጀመሪያው አጋማሽ ውስጥ ዝናብ በተቋረጠባቸው ነገር ግን በቀደመው ነሐሴ ወር የተሻለ የዝናብ ሁኔታ በነበራቸውና በተለይ ደግሞ ከወሩ አጋማሽ በኋላ የተወሰነ ዝናብ ባገኙ ቦታዎች የዝናቡ መቋረጥ በሰብሎች ቀጣይ እድገትም ሆነ በአጠቃላይ የሰብል ልማት እንቅስቃሴ ላይ የጎላ ተፅእኖ አለማሳደሩን፣

- ይህ በዚህ እንዳለ በወሩ በአንዳንድ ቦታዎች የደረሱ የመኸር ሰብሎችን የመሰብሰብ ተግባር የተከናወነ ሲሆን በተለይ በሁለተኛው የወሩ አጋማሽ ውስጥ በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች በነበረው ዝናብ በቆላማና በሌሎችም አንዳንድ አካባቢዎች ቀድመው በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት ከመድረሱ በፊት የመሰብሰብ ተግባር መከናወኑን የተሰበሰቡት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

- በሌላ በኩል በወሩ የመጀመሪያው አጋማሽ ውስጥ በተከሰተው የዝናብ መቋረጥ የእርጥበት እጥረት ባጋጠማቸው አንዳንድ ቦታዎች ሁኔታው ከመኸሩ ዝናብ አገባብ፣ መጠንና ስርጭት አለመስተካከል ጋር ተዳምሮ መደበኛ የሰብል ልማት ተግባራት መስተጓጎሉንና ቀደም ብለው የተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰብሎች የእርጥበት ችግር እንደገጠማቸውና አልፎ አልፎም እስከ መድረቅ ደረጃ መድረሳቸው ወይም ለእንስሳት መኖ እንዲውሉ መደረጋቸው ተጠቁሟል፡፡ ሆኖም ከወሩ አጋማሽ በኋላ በነበረው ዝናብ የተገኘው እርጥበት ሁኔታውን በማሻሻሉ በሰብል ምርት ላይ ሊደርስ ይችል የነበረውን ጉዳት በጉልህ እንደሚቀንሰው ከክትትል መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

በክልሎች የነበረውን ሁኔታ በተመለከ፡-

- በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ክልል በሲዳማ፣ ጌዴኦ፣ ወላይታ፣ ሀዲያ፣ ከፋ፣ ጋሞጎፋ ዞኖችና በባስኬቶና ኮንታ ልዩ ወረዳዎች የበልግ ሰብሎች በመድረቅና በመሰብሰብ ላይ መሆናቸው፣ በክልሉ የረጅም ጊዜ የመኸር አገዳ ሰብሎች በሲዳማ፣ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ጌዴኦ ዞኖችና ሀላባ ልዩ ወረዳ ከአበባና ፍሬ መሙላት እስከ እሸት የእድገት ደረጃዎች ላይ የሚገኙ መሆናቸው፣ ሌሎች የመኸር ሰብሎች ደግሞ ከላይ የተጠቀሱትን የክልሉ አካባቢዎች ጨምሮ በወላይታ፣ ከፋ፣ ጋሞጎፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ማጂ፣ ዳውሮና ስልጤ ዞኖችና በየም ልዩ ወረዳዎች ከእድገት እስከ አበባና ፍሬ መሙላት ደረጃዎች ላይ መሆናቸው፣ ደ/ኦሞ ዞንና ኮንሶ፣ አማሮና ደራሼ ልዩ ወረዳዎችን ጨምሮ በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች የዘር ስራ በመከናወን ላይ ሲሆን ቀደም ሲል የተዘሩትም ሰብሎች በቡቃያ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸው፣

- በኦሮሚያ ክልል ደ/ምዕ/ሸዋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጉጂ፣ ምዕ/ወለጋ፣ ጂማ፣ ቄለም ወለጋ፣ አርሲና ሰ/ሸዋ ዞኖች የመኸር ሰብሎች ከአበባ እሰከ ፍሬ መሙላትና እሸት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ በጉጂ ዞን የዘር ስራ በመከናወንና ቀደም ሲል የተዘሩትም ሰብሎች በቡቃያ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸው፣

- በትግራይ ክልል ምዕራባዊ፡ ሰሜናዊ ምዕራብ፣ ምስራቃዊ፣ ደቡባዊ ምስራቅና ደቡባዊ ዞኖች ሰብል በማበብና ፍሬ በመሙላት ላይ የሚገኝ መሆኑ፣ ሆኖም በእነዚህ አካባቢዎች ከነሀሴ ወር መጨረሻ ጀምሮ እስከ መስከረም አጋማሽ የመኸሩ ዝናብ በመቋረጡ ምክንያት ጉዳት ይደርሳል የሚል ስጋት የነበረ ቢሆንም ከወሩ አጋማሽ በኂላ የተገኘው እርጥበት በሰብል ምርት ላይ ሊደርስ የነበረውን ጉዳት በጉልህ እንደሚቀንሰው መረጃዎች መጠቆማቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከመስከረም አጋማሽ በኂላ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች የጣለው ዝናብ በደረሱ ሰብሎች ጉዳት ከማድረሱ በፊት በደቡባዊ ዞን ህንጣሎ ዋጅራትና ራያ አዘቦ ወረዳዎች፣ በማዕከላዊ ዞን ታህታይ ማይጨው፣ አህፈሮም፣ በሰሜን ምዕራብ ዞን አስገደ ድምብላ፣ መደባይ ዛና፣ በምስራቃዊ ዞን ጋንታ አፈሹም፣ ክለተአውላእሎና አፀቢ.ወንበርታ ወረዳዎች የሰብል አጨዳ በመከናወን ላይ መሆኑ፣ እንዲሁም በተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች (ለምሳሌ በሰሜን ምዕራብ ዞን ፀለምቲ ወረዳና በምስራቃዊ ዞን ክለተአውላእሎ ወረዳ) የውሃ ማቆርና የመስኖ ስራዎች ተጠናክረው የቀጠሉ መሆናቸው፣

- በአማራ ክልል የመኸር ተጠቃሚ በሆኑ በክልሉ ምእራባዊ አካባቢዎች በዘር ለመሸፈን ከታቀደዉ 3,873,183 ሄ/ር መሬት ዉሰጥ 3,922,262 ሄ/ር መሬት ታርሶ 3,828,801 ሄ/ር መሬት በተለያዩ ሰብሎች ዘር መሸፈኑና ይህም በጠቅላለው ሊታረስ ከታቀደዉ መሬት ከ1 በመቶ በላይ ብልጫ ያለውና እንዲሁም ከታረሰው መሬት 99 በመቶ በዘር የተሸፈነ መሆኑ፣ ሰብሎቹም በቡቃያ (ሽንብራና ጓያ)፣ በእድገት፣ በአበባና አልፎ አልፎም ፍሬ በመሙላትና በመታጨድ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ፣ እስካሁን ድረስ በሰሜን ወሎ፣ ሰ/ሸዋ፣ አዊ፣ ምዕራብ ጎጃም፣ ዋግ ሕምራ፣ ሰ/ጎንደርና ኦሮሚያ ዞኖች ገብስ (84.14 ሄ/ር) ጤፍና በቆሎን ጨምሮ የተለያዩ ሰብሎች የታጨዱ መሆኑ፣ እንዲሁም በሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ፣ ደቡብ ጎንደር፣ ሰ/ጎንደርና ምዕራብ ጎጃም ዞኖች የተለያዩ ቦታዎች የዘር ሥራ በመከናወነ ላይ መሆኑ፣



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመኸር በቆሎና ሰሊጥ ለአጨዳ በመድረስ ላይ፣ ማሽላ ከእድገት ፍሬ እስከ ማፍራት ደረጃ ላይ መሆኑ፣

- በጋምቤላ ክልል በነሀሴ ወር የተዘራ ማሽላ በብቅለትና በቡቃያ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በቆሎ በርጥበት እጥረት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ፣ ውሃ ሸሽ መሬቶችን ለመዝራት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ፣

- በሐረሪ ክልል ለውዝ በመሰብሰብ ላይ ሲሆን በእርጥበት እጥረት ምክንያት በቆሎና ማሽላ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ማሽላ በከፊል ለመኖነት እየተነሳ መሆኑ፣

- በድሬዳዋ አስተዳደር ማሽላ ባብዛኛው በቡቃያ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በእርጥበት እጥረት ምክንያት ጠውልጎ መገኘቱ፣ በአስተዳደሩ በ13 ቀበሌዎች ውስጥ ተዘርቶ ከነበረው የበቆሎ ሰብል በ2 ቀበሌዎች በተሻለ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ሲሆን በ11 ቀበሌዎች ውስጥ የነበረው ግን በእርጥበት እጥረት በመጎዳቱ ታጭዶ ለእንስሳት መኖ አገልግሎት መዋሉ፣

- በሶማሌ ክልል በጂጂጋ አካባቢ ሰብል በተሻለ ሁኔታ የሚገኝ ሲሆን በሸንሌ ዞን ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ግን በካራን ዝናብ መዛባት ምክንያት አነስተኛ ብቅለትና ደካማ አቋም የሚታይበት መሆኑ፣

በጥቅሉ እስካሁን በነበረው የመኸር ዝናብ ሂደት በአብዛኛዎቹ የመኸር ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሰብል ልማት ሥራ እንቅስቃሴ አመች ሁኔታን በመፍጠሩ፣ ባሳለፍነው መስከረም ወር ሁለተኛው አጋማሽ በብዙዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች የዘነበው ዝናብ በወሩ የመጀመሪያው አጋማሽ ሰፍኖ የነበረውን ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ በማርገቡና ከዚሁ ጋር በተያያዘም በአንዳንድ ቦታዎች ተከስቶ የነበረውን የእርጥበት እጥረት በማሻሻሉ፣ በቀዳሚው የበልግ ወቅት በአብዛኛዎቹ የበልግ ተጠቃሚ አካባቢዎች በነበረው የዝናብ መዛባት ምክንያት የተገለበጡና ከጅምሩ ያልተዘሩ አብዛኛዎቹን መሬቶች በዘር እንዲሸፈኑ በማስቻሉ፣ አጠቃላይ የምርት ግብአት አቅርቦትና አጠቃቀም በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች በተፈለገው ደረጃ በመተግበሩ፣ በተጨማሪም እስካሁን ድረስ በሰብል ላይ የጎላ ጉዳት ያስከተለ የፀረ ሰብል ተባዮች ክስተት ባለመኖሩ፣ ሁኔታው ለ2001/02 የመኸር ሰብል ምርትና ምርታማነት ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ከወዲሁ ይገመታል። ይሁንና በቀጣዮቹ የበጋ ወራት የመኸሩ አዝመራ ተሰብስቦ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የሚኖረው የአየር ሁኔታ ቀጣይ መደበኛ የሰብል ልማት ተግባራትን በወቅቱ ለማከናወን የሚያስችል መሆኑ ወሳኝ ነው።

## 2.2. የተዛማች ፀረ-ሰብል ተባዮች ክስተት ሁኔታ

- **የበረሐ አንበጣ**

በወሩ በየትኛውም የሀገሪቱ አካባቢ የበረሃ አንበጣ ወረርሽኝ ስለመከሰቱ የቀረበ ሪፖርት የለም።



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 ኢ.አ

- ግሪሳ ወፍ

ከመስከረም ወር ሶስተኛው ሳምንት ጀምሮ የግሪሣ ወፍ ወረርሽኝ በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን በመቂ፣ ዝዋይና አዳሚቱሉ ወረዳ እንዲሁም በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ክልል ስልጤ ዞን ላንፋሮ ወረዳ ተከስቶ በሰብል ላይ ጉዳት ሳያደርስ መከላከል መቻሉ ታውቋል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች በጠቅላላው በ100 ሄክታር የወፍ ማደሪያ ስፍራዎች በነበረ ብዛቱ 6 ሚሊዮን የሚገመት የወፍ መንጋ ላይ 200 ሊትር ፀረ-ወፍ ኬሚካል በመርጨት የመከላከል ስራው መከናወኑ ታወቋል፡፡

- ተምች

የተምች ተባይ ክስተት በመስከረም ወር የተለመደ ባለመሆኑ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል አልታየም፡፡

## 2.3. የእንስሳት ሁኔታ

ባሳለፍነው መስከረም ወር ሁለተኛው አጋማሽ በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች የነበረው የዝናብ ሁኔታ በወሩ የመጀመሪያው አጋማሽ ውስጥ ሰፍኖ የነበረውን ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ በማርገብ ለውሃ አቅርቦትና ለግጦሽ መሻሻል አስተዋፅኦ እንደነበረው በክትትል የተሰበሰቡ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከበልጉ ዝናብ መዛባትና ከክረምቱ ዝናብ ዘግይቶ መጀመር ጋር በተያያዘ በአንዳንድ አካባቢዎች አጋጥሞ በነበረው የእርጥበት እጥረት ምክንያት የግጦሽ እና/ወይም የውሃ እጥረቱ አሁንም በበቂ ሁኔታ ያልተቃለለባቸው አካባቢዎች መኖራቸው ተጠቁሟል፡፡ እነዚህም አካባቢዎች:-

- በደቡብ ብ/ብ/ህ/ ክልል በወላይታ ዞን ሁምቦና ዱጉና ፋንጎ ወረዳዎች፣ በጋሞጎፋ ዞን ምዕ/አባያ፣ ዛላ፣ ከምባ፣ ቦንኬ፣ ኡባ ደ/ፀሀይና ደራማሎ ወረዳዎች፣ በደ/ኦሞ ዞን ከደቡብና ሰሜን አሪ ወረዳዎች በስተቀር በሌሎቹ ወረዳዎች፣ በቡርጂ ልዩ ወረዳ፣
- በትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን በራያ አዘቦ፣ አላማጣና ሕ/ዋጅራት ወረዳዎች፣ በምስራቃዊ ዞን ክልተአውላእሎ ወረዳ ሲሆኑ፣ እስካሁን ድረስ ከራያ አዘቦ ወረዳ 2340 ከብቶች፣ ከአላማጣ ወረዳ 1581 ከብቶች መኖ ፍለጋ ወደ አፋር ክልልና ወደ አማራ ክልል ዋግ ህምራ ዞን መጓዛቸው፣
- በአማራ ክልል በደ/ወሎ ዞን አርጎባ ወረዳ፣ በሰ/ወሎ ዞን በሐብሩና ጎባላፍቶ ወረዳዎች እንዲሁም በዞኑ ቆላማ አካባቢዎች፣ በዋግ ኅምራ ዞን ዝቋላና አበርገሌ ወረዳዎች፣
- በኦሮሚያ ክልል በምስ/ሀረርጌ ዞን ሚዳጋ፤ መዩ እና ጎሎ ኦዳ ወረዳዎች፣ በባሌ ዞን በወ/ደጋና ቆላ አካባቢዎች፣ በአርሲ ዞን ጎሎልቻ፤ ሴሩና አሚኛ ወረዳዎች፣ በቦረና ዞን ሞያሌ፣ ሚዮ፣ ዲሎና ድሬ ወረዳዎች፣ በምዕ/ሐረርጌ ዞን ቆላማ አካባቢዎች፣ በምስ/ሸዋ ዞን ፈንታል ወረዳ
- በሶማሌ ክልል በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች የመኖ እጥረት እንዲሁም በአፍዴር፣ ጎዴ፣ ሊበን፣ ደገሀቡር፣ ፊቅ፣ ቆራሄ፣ ሺንሌና ዋርዴር ዞኖች ብዙ አካባቢዎች የውሃ እጥረት መኖሩ፣
- በአፋር ክልል ዞን 2 አንዳንድ ቦታዎች፣
- በድሬዳዋ አስተዳደር አብዛኛዎቹ ቀበሌዎችን የሚያካትቱ መሆናቸው ከክትትል መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፖ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

### 2.4. የደን እሳት ቃጠሎ ክስተት

- በየትኛውም የክትትል መረጃ በተሰበሰበባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች በወሩ የደን ቃጠሎ ስለመከሰቱ የቀረበ ሪፖርት የለም፡፡

### 2.5. የተዛማች የእንስሳት በሽታዎች ፍንዳታ ክስተት

- ከየትኛውም የክትትል መረጃ በተሰበሰበባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች በወሩ የእንስሳት በሽታ ፍንዳታ ስለመከሰቱ የቀረበ ሪፖርት የለም፡፡

### 2.6. የሌሎች አደጋዎች ክስተት

ባሳለፍነው ወር በሀገሪቱ አንዳንድ ቦታዎች በረዶ በቀላቀለ ከባድ ዝናብ፣ በጎርፍና በመሬት መደርመስ ክስተቶች በሰብልና በእንስሳት ላይ የተለያየ መጠን ያለው ጉዳት የደረሰ መሆኑን የክትትል መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም መሰረት፡-

- በደቡብ ብ/ብ/ህ/ ክልል በጋሞጎፋ ዞን ቦንኬ ወረዳ የተከሰተ የጎርፍ አደጋ 23 ሄ/ር ሰብል ላይ፣ በቁጫ ወረዳ በረዶ ቀላቅሎ የጣለ ዝናብ በ400 ሄ/ር ሰብል ላይ፣ በባስኬቶ ልዩ ወረዳ በሻንካ ቀበሌ በ17 ሄ/ር ሰብልና በ36 እንስሳት ላይ፣

- በትግራይ ክልል አነስተኛ የዝናብ መጠንና የተዛባ ስርጭት በነበራቸው የደቡባዊ፣ የደቡባዊ ምስራቅና ምስራቃዊ ዞኖች በሚገኙ ዘጠኝ ወረዳዎች ውስጥ 21,865 ሄ/ር የተለያዩ ሰብሎች በድርቅ፣ በጎረፍና በበረዶ ክስተቶች፣ በሰሜናዊ ምዕራብ ዞን በተከሰተ የጎርፍና የበረዶ አደጋ በመደባይ ዛና ወረዳ 71.5 ሄ/ር ሰብል፣ በታ/ቆራሮ ወረዳ በ1327 ሄ/ር ሰብል፣ በ1498 በጎችና ፍየሎች፣ በ241 ከብቶችና በ38 የጋማ ከብቶች ላይ፣

- በአማራ ክልል በደ/ጎንደር ዞን ሰማዳ ወረዳ በጣለዉ በረዶ 253 ሄ/ር ሰብል ላይ፣ በደ/ወሎ ዞን በወረባቡ ወረዳ ውስጥ የመሬት መደርመስ በ42 ሄ/ር መሬት ላይ፣ በምስራቅ ጎጃም ዞን በ4 ወረዳዎች ውስጥ በተከሰተ በረዶ በ402 ሄ/ር ሰብል ላይ፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን በጫጫ ወረዳ ውስጥ በተከሰተ በረዶ በ152 ሄ/ር ሰብል ላይ፣

- በኦሮሚያ ክልል በተከሰተ የበረዶ አደጋ በደ/ምዕ/ሸዋ ዞን በበቾ ወረዳ በ125 ሄ.ር ሰብል ላይ እና በኢሉአባቦራ ዞን በዳሪሙ ወረዳ በ5 ቀበሌዎች 239 ሄ/ር ሰብል ላይ ጉዳት መድረሱን ከየአካባቢው ከተገኘ መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

## ለ. የጥቅምት ወር የአየር ሁኔታ አዝማሚያና በአርሶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩና አርብቶ አደሩ ሊወሰዱ የሚገባቸው ተከታታይ እርምጃዎች

### 1. የጥቅምት ወር የዓየር ሁኔታ አዝማሚያ

ከብሄራዊ የሜቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በተገኘ እ.አ.አ. የጥቅምት 2009 የአየር ሁኔታ አዝማሚያ መረጃ መሰረት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ ሰጪ ክስተቶች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚይዙ፣ የሀገሪቱ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ቆላማ አካባቢዎች እንዲሁም የምእራብና የደቡብ ምእራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ዝናብ ማግኘታቸውን የሚቀጥሉ ሲሆን በሌላ በኩል የሰሜን፣ የሰሜን ምሥራቅና የመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች በደረቅ የአየር ሁኔታ ተጽእኖ ስር እንደሚሆኑና ከዚህም ጋር በተያያዘ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ መጠናከር እንደሚጀምር ተጠቁሟል።

በወሩ ጋምቤላ፣ ምእራብ ኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች መደበኛ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፣ ምሥራቅ አማራ፣ ምሥራቅ ትግራይ፣ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች የባሌና የአርሲ አካባቢዎችን ጨምሮ እንዲሁም አፋር ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ ያገኛሉ። በሌላ በኩል ምእራብ ትግራይና አማራ፣ የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ሰሜናዊ አጋማሽ ከመደበኛው ያነሰ ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ መሆኑን በኤጀንሲው መረጃ ተመልክቷል።

### 2. በአርሶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩና አርብቶ አደሩ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች

#### 2.1. ሰብል ልማትን በተመለከተ

በጥቅምት ወር የሚከናወኑት የሰብል ልማት ሥራ ተግባራት ከቦታ ቦታ የተለያዩና ቀደም ባሉት ወራቶች ከተከናወኑት ተግባራት ጋር ተከታታይነት ያላቸው እንደመሆናቸው መጠን በወሩ ከሚኖረው የዓየር ሁኔታ አኳያ አርሶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩና የእነርሱ አጋዥ የሆኑ የግብርና ልማት ባለሙያዎች ለሚከተሉት ዓበይት የሰብል ልማት ሥራ ተግባራት ተገቢውን ትኩረት መስጠት ይጠበቅባቸዋል:: ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራትም:-

- በጥቅምት ወር ከሚከናወኑት ዐበይት የሰብል ልማት ተግባራት መካከል ዋነኛው የደረሱ ሰብሎችን የመሰብሰብ ተግባር ነው:: ስለሆነም በዓየር ሁኔታ አዝማሚያ መረጃው እንደተመለከተው በወሩ መደበኛና ከመደበኛው የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ በተጠቀሙ የሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች እንዲሁም ባሳለፍነው መስከረም ወር ከኤጀንሲው በተገኘው የበጋው ወቅት የዓየር ሁኔታ አዝማሚያ ጠቋሚ መረጃም እንደተመለከተው በያዝነው የበጋው ወቅት በመደበኛው ሁኔታ ደረቅ የአየር ሁኔታ በሚዘወተርባቸው በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊከሰት እንደሚችል የተጠቀመ በመሆኑ አርሶ አደሩ የራሱንና የቤተሰቡን ጉልበት በማስተባበር በማንኛውም ጊዜ ሰብል ለመሰብሰብ አመች በሚሆን የዓየር ሁኔታ በመታገዝ የደረሱ ሰብሎችን ፈጥኖ በመሰብሰብ እስኪወቃ ድረስ በዝናብ ጉዳት ሊደርስበት በማይችል መልኩ መከመር ይጠበቅበታል:: እንደአስፈላጊነቱም በየደረጃው የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማስተባበር በዘመቻ መልክ የደረሱ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ከወዲሁ አቅዶ መንቀሳቀሱ ተገቢ በመሆኑ የሚመለከታቸው ክፍሎች ለዚህ አቢይ ተግባር ተገቢውን ትኩረት መስጠት ይጠበቅባቸዋል::



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 ኢ.አ

- ሰብል ከተሰበሰበ በኋላ ለረዥም ጊዜ ክምሮ ማቆየት ለዝናብና ለተባይ ጥቃት ስለሚዳርገው በተቻለ መጠን በማንኛውም ጊዜ በሚኖረው ፀሐያማ የዓየር ሁኔታ በመታገዝ ንፅህናው በተጠበቀ አውድማ ላይ በወቅቱ መውቃቱ አስፈላጊ ነው::

- ሰብል እንደተሰበሰበ ማሳን ወዲያውኑ ማረስ ለተሟላ የማሳ ዝግጅትና ሰብልን ከነፍሳት ተባይ፣ ከበሽታና ከአረም ጥቃት መከላከል ከሚያስችሉ ዘዴዎች አንዱ በመሆኑ አርሶ አደሩ በወሩ ይህን ዐብይ የእርሻ ተግባር ለማከናወን አመች ሁኔታን በሚፈጥር የዓየር ሁኔታ በመታገዝ በወቅቱ ይህን ማከናወን ይጠበቅበታል::

- ጥቅምት ዋነኛ የዝናብ ወር በሆነባቸው ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲሁም ዝናብ ማግኘታቸውን እንደሚቀጥሉ የተተነበዩ የምእራብና የደቡብ ምእራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ዝናቡ በሚፈጥረው ምቹ ሁኔታ በመጠቀም አርሶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ የዘር ስራና ሌሎችም ወቅታዊ የግብርና ተግባራትን ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

- በወሩ ውስጥ የሚጠበቀው ዝናብ ከመደበኛው ጋር ያለመስተካከልና (ምስራቅ አማራ፣ ምስራቅ ትግራይ፣ ባሌና አርሲ አካባቢዎች እንዲሁም አፋር) በአንዳንድ ቦታዎች ላይ (ምዕራብ ትግራይና አማራ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሰሜናዊ ክፍል) አነስተኛ እንደሚሆን እንዲሁም በነዚሁ አካባቢዎች በበጋው ወቅት የሚኖረው ዝናብ በአመዛኙ አነስተኛ እንደሚሆን የወሩና የወቅቱ የዓየር ሁኔታ አዝማሚያ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ስለሆነም በዚሁ ምክንያት በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ሊከሰት የሚችለውን አሉታዊ ተፅእኖ ለመቀነስና ለመቋቋም በማንኛውም ጊዜ የሚገኘውን እርጥበት የተለያዩ የውሃ ማቆር ዘዴዎችን ተጠቅሞ በመሰብሰብ ለግብርና ሥራ ተግባር ለማዋል ጥረት ማድረጉ አማራጭ የለውም::

- በበጋ ወቅት ውሃ ገብ በሆኑ አካባቢዎች አነስተኛ የመስኖ ልማት እንቅስቃሴ በስፋት የሚካሄድበት ጊዜ በመሆኑ በያዝነው ወር የመስኖ ቦዮችን ማፅዳት፣ የማሳ ዝግጅትን ማከናወን፣ የዘር አቅርቦትን ዝግጅት ማድረግና የችግኝ ማፍላት እንቅስቀሴዎችን በወቅቱ ማከናወን በአርሶ አደ የተለየ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራት ይሆናሉ::

### 3. 2.2. ተዛማች ፀረ-ሰብል ተባዮችን በተመለከተ

- **ተምች**

በጥቅምት ወር የተምች ወረርሽኝ የሚከሰትበት ወቅት ባለመሆኑ ስጋት አይኖርም::

- **የበረሃ አንበጣ**

ባለንበት ጥቅምት ወር የአንበጣ ወረርሽኝ ክስተት ስጋት ያለመኖሩን ከመ/ቤታችን እንስሳትና እፅዋት ጤናና ጥራት ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ከተገኘ መረጃ መረዳት ተችሏል። ሆኖም ተባዩ ሊከሰትባቸው ይችላል ተብለው በሚጠረጠሩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሁሉ የሚመለከታቸው አካላት የክትትልና የአሰሳውን ስራ አጠናክረው በመቀጠል ተባዩ እንደታየ ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል።

- **ግሪሣ ወፍ**

ከመስከረም ወር ሶስተኛው ሳምንት ጀምሮ የግሪሣ ወፍ ወረርሽኝ በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን በመቂ፣ ዝዋይና አዳሚቱሉ ወረዳ እንዲሁም በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ክልል ስልጤ ዞን ላንፋሮ



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

ወረዳ ተከስቶ በሰብል ላይ ጉዳት ሳያደርስ መከላከል መቻሉ ታውቋል፡፡ ባለንበት ጥቅምት ወርም የግሪሣ ወፍ ወረርሽኝ በመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በምስራቅ የሀገሪቱ ቆላማ ስፍራዎች እንዲሁም በደቡብ ምስራቅ የአማራ ክልል ቆላማ ስፍራዎች ሊከሰት ስለሚችል በእነዚህ አካባቢዎች የሚገኙ አርሶ አደሮችና የግብርና ልማት ባለሙያዎ ክትትልና አሰሳ በማድረግ ወፉ መከሰቱ ሲረጋገጥ ለሚመለከተው ክፍል በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ኖርባቸዋል፡፡

## 2.1 የእንስሳት ሁኔታ

በወሩ ውስጥ የሚጠበቀው ዝናብ ከመደበኛው ጋር ያለመስተካከልና (ምስራቅ አማራ፣ ምስራቅ ትግራይ፣ ባሌና አርሲ አካባቢዎች እንዲሁም አፋር) በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አነስተኛ (ምዕራብ ትግራይና አማራ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሰሜናዊ ክፍል) እንደሚሆን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ስለሆነም በዚሁ ምክንያት እንስሳት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ችግር ለመቀነስና ለመቋቋም በአሁኑ ጊዜ በየአካባቢዎቹ ያለውን የመኖና የውሃ ክምችት በቁጠባ መጠቀሙ አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ በማንኛውም ጊዜ የሚገኘውን እርጥበት የተለያዩ የውሃ ማቆር ዘዴዎችን ተጠቅሞ በመሰብሰብ ለእንስሳት አቅርቦት ለማዋል ጥረት ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ መኽር አምራች በሆኑ አካባቢዎች ወቅቱ የምርት ስብሰባ በመሆኑ ለእንስሳት መኖ በቂ ተረፈ ምርት የሚገኝ በመሆኑ ይህንኑ በአግባቡ በመሰብሰብና በማከማቸት በቁጠባ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.4. የደን እሳት ቃጠሎ ክስተት

በመደበኛ ሁኔታ የበጋ ደረቅና ፀሀያማ የአየር ሁኔታ ለደን እሳት መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ ባለንበት ጥቅምት ወርም የደን ቃጠሎ እንዳይከሰት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

## 4. ማጠቃለያ

በአጠቃላይ በያዝነው ጥቅምት ወር ከሚኖረው የዓየር ሁኔታ አዝማሚያ አኳያ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ዙሪያ መወሰድ የሚገባቸውን ተከታታይ እርምጃዎች ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልኩ በወቅቱ ተግባራዊ እንዲደረጉ በየደረጃው የሚገኙ የግብርና ባለሙያዎች አስፈላጊውን ሙያዊ እገዛና የተጠናከረ የምክር አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 ኢ.አ